# ሰርቫይቨር ሊደርሺፕ ፈንድን ማመልከቻ አስመልክቶ ተደጋጋሚ የተጠየቁ ጥያቄዎች እና የተሰጡ ማብራሪያዎች

የዚህ ፈንድ አላማ ከዘመናዊ ባርነት በህይወት በተረፉ ሰዎች ወይንም የብዝበዛ (ለምሳሌ፡ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ አስገዳጅ የጉልበት ስራ፣ አስገዳጅ የሰዎች ጉልበት ብዝበዛ ፣ አስገዳጅ ጋብቻ የሕይወት ተሞክሮ ባላቸው ሰዎች የሚመሩ ድርጅቶችን መደገፍ ነው። በኢትዮጵያ፣ በኡጋንዳ ወይም በታንዛኒያ የሚገኙ ከዘመናዊ ባርነት በህይወት በተረፉ ሰዎች የሚመሩ ድርጅቶች ለማመልከት እንኳን በደህና መጣችሁ።

- **ማነው የሚያመለክተው**

  በኢትዮጵያ፣ በኡጋንዳ እና በታንዛኒያ የተመዘገቡ (ወይም በመመዝገብ ላይ ያሉ) ድርጅቶች ለዚህ ዙር ማመልከት ይችላሉ። ለማመልከት ድርጅቶች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ከዘመናዊ ባርነት በሕይወት የተረፉ እና ተለይተው የሚታወቁ ሰራተኞችን ወይም የብዝበዛ የሕይወት ተሞክሮ ያሏቸው ሰረተኞችን በአመራር ባታዎች (ለምሳሌ፡ ዳይሬክተር፣ ዋና ስራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ ስራ አስኪያጅ) ላይ የሚሰሩ ሲኖሮት ብቻ ነው።

- **በአሁኑ ሰዓት የፍሪደም ፈንድ አጋር ድርጅት ነን - ማመልከት እንችላለን?**

  **ማመልከት አይችሉ፣** የፍሪደም ፈንድ አጋር ድርጅቶች ለዚህ ፈንድ ማመልከት አይችሉም። ለበለጠ መረጃ እባክዎን ፍሪደም ፈንድ ተወካይ ሆኖ ከድርጅትዎ ጋር በቅርበት ግንኙነት የሚያደርገዉን ተወካይ ያግኙ፣ ወይም እርግጠኛ ካልሆኑ በዚህ **SLF@freedomfund.org** ኢሜይል ይላኩ።

- **ለተመረጡት ድርጅቶች የሚሰጠው ድጋፍ በገንዘብ  ምን ያህል ነው?**

  በዚህ ዙር፣ ለሚመረጡ ድርጅቶች የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ እስከ $20,000 (ሀያ ሺህ የአሜሪካ ዶላር) ነው።

- **ከዘመናዊ ባርነት በህይወት በተረፉ ሰዎች የሚመራ ድርጅት ማለት ምን ማለት ነው?**

ከዘመናዊ ባርነት በህይወት በተረፉ ሰዎች የሚመራ ድርጅት የሚባሉት በድርጅቱ ውስጥ በአመራር ቦታዎች ላይ ከዘመናዊ ባርነት በህይወት በተረፉ ሰራተኞች ወይም የብዝበዛ የሕይወት ተሞክሮ ያሏቸው ሰራተኞች ያለው ድርጅት ማለት ነው። ሰራተኛው በድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ የአመራር ቦታ ይዟል የሚባለው የድርጅቱን ስትራቴጂ፣ ተግባራት እና/ወይም ፋይናንስን ጉዳዮችን በተመለከተ የመወሰን ስልጣን ሲኖራቸው ነው። ይህ ከፍተኛ አመራሮችን፣ ዳይሬክተሮችን፣ ምክትል ዳይሬክተሮችን እና የዲፓርትሜንት ኃላፊዎችን ሊያካትት ይችላል።

- **ከዘመናዊ ባርነት በህይወት በተረፉ ሰዎች ወይም “የብዝበዛ የሕይወት ተሞክሮ ያላቸው ሰዎች” ስንል ምን ማለታችን ነው?**

ለዚህ ፈንድ ዓላማ “የብዝበዛ የሕይወት ተሞክሮ” ማለት በአስገዳጅ ለጉልበት ሥራ፣ ለሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ፣ ለአስገዳጅ የሰዎች ጉልበት ብዝበዛ፣ ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ለግዳጅ ጋብቻ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ማለት ነው።

- **የሚያመለክቱት ምን አይነት ድርጅቶች ናቸው?**

ፈንዱ በዋነኝነት የዘመናዊ ባርነት ችግሮችን (ለምሳሌ፡ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ አስገዳጅ የጉልበት ሥራ፣ አስገዳጅ የሰዎች ጉልበት ብዝበዛ እና ያለእድሜ ጋብቻ) ለመፍታት ለሚሰሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን መደገፍ ነው። ከዘመናዊ ባርነት በህይወት በተረፉ ሰዎች የሚመሩ የሰራተኞች ህብረት ወይም የማህበራዊ ድርጅቶች ከግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። የቤተ እምነት ድርጅቶች ከፍሪደም ፈንድ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣሙ ከሆነ፣ ለዚህ ፈንድ ማመልከት ይችላሉ።

- **ይህ ፈንድ የሚሰጠው በድርጅታችን ውስጥ የሚገኙትን ከዘመናዊ ባርነት ወይም ከብዝበዛ በሕይወት የተረፉ ሰራተኞችን ለመደገፍ ነው ወይስ መላ ድርጅታችንን ለመደገፍ ነው?**

  ይህ የገንዘብ ድጋፍ ድርጅቱን በአጠቃላይ ለመደገፍ ወይም ድርጅቱ የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልገዋል ብሎ ያመነበትን ስራ ሁሉ ላይ ሊያውል ይችላል። ይህም ኦፕሬሽኖች፣ ፕሮግራሞች፣ የቢሮ ክራይ ክፍያዎች፣ የቴክኖሎጂ ግዢዎች፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል። የድርጅቱን ሰራተኞችን (ከዘመናዊ ባርነት ወይም ከብዝበዛ በሕይወት የተረፉትን) ብቻ ለመደገፍ የሚሰጥ ድጋፍ አይደለም።

- **ድርጅታችን በዚህ ፈንድ በአንድ ግዜ ከአንድ በላይ ፈንድ ለማግኘት ማመልከት ይችላል?**

  ይህ ፈንድ በተቻለ መጠን ብዙ ድርጅቶችን ለመደገፍ ያለመ እንደመሆኑ መጠን፣ እያንዳንዱ አመልካች ድርጅት በዚህ ዙር ለአንድ የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ነው ማመልከት የሚችሉት።

- **ይህ የአንድ ጊዜ ፈንድ ድጋፍ ነው ወይስ በሚቀጥለው ዓመት እንደገና ማመልከት እችላለሁ?**

  ለግዜው ይህ ፈንድ ለአንድ ድርጅት የአንድ ጊዜ የድጋፍ ፈንድ ነው፣ ስለዚህ ለተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ እንደገና በሌላኛው ማመልከት አይችሉም።

- **የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ ምን ላይ ነው መጠቀም የሚንችለው?**

  ይህ ፈንድ ያለተገደበ ድጎማ ነው፤ ይህ ማለት ድርጅቱ የድርጅቱን ግቦችን ለማሳካት ያስችለኛል ብለው ላመኑበት ለማንኛውም ነገር ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ገንዘቡን ፍላጎት በሚያዩበት ቦታ ሁሉ ላይ እንደሚጠቀሙ እንደ ድርጅት እናምናለን።

- **ከዚህ የገንዘብ ድጋፍ ምን አይነት ሪፖርት ይጠበቃል?**

  የዚህ ፈንድ ባህሪ በተቻለ መጠን በተቀባዮች ላይ ያለውን አስተዳደራዊ ሸክም ለመቀነስ ነው፤ ስለዚህ የሚጠበቀው ሪፖርት ዝቅተኛ ነው። የምንጠይቀው ነገር ከስድስት ወራት በኋላ ስሆን፣ የተቀበሉትን ገንዘብ ምን ምን ላይ እንዳዋሉ እና ተልኮአችሁን እንዴት እንደደገፍ የሚገልጽ የኢሜይል፣ የደብዳቤ፣ የቪዲዮ ወይም የድምጽ ማስታወሻ እንዲልኩልን ነው።

- **ድርጅታችን በኢትዮጵያ፣ በኡጋንዳ ወይም በታንዛኒያ ውስጥ ባይገኝ ማመልከት እችላለሁ?**

  **ማመልከት አይችሉም**፣ በዚህ ዙር የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠው በኢትዮጵያ፣ በኡጋንዳ ወይም በታንዛኒያ ውስጥ ለሚገኙ በዘመናዊ ባርነት እና ብዝበዛ በሕይወት በተረፉ ሰዎች የሚመራ ድርጅቶች ብቻ ነው። ወደፊት በሌላ የገንዘብ ድጋፍ በሌሎች አካባቢዎች እንጀምራለን ብለን እናምናለን፤ ስለዚህ ማስታወቂያዎቻችንን በድረ-ገጻችን አማካይነት ይከታተሉ።

- **ድርጅታችን በኢትዮጵያ፣ በኡጋንዳ ወይም በታንዛኒያ ውስጥ ባይገኝም ነገር ግን በእነኚህ አገራት ውስጥ ፕሮግራሞች ብኖሩን፣ ማመልከት እችላለን?**

  **ማመልከት አይችሉም**፣ ይህ ፈንድ በኢትዮጵያ፣ በኡጋንዳ ወይም በታንዛኒያ ውስጥ ላሉት የአገር በቀል ድርጅቶችን ብቻ ከግምት ውስጥ ያስገባ ፈንድ ነው። በእነዚህ አገሮች ውስጥ የሚሠሩ ነገር ግን የተመዘገቡ ወይም ዋና መሥሪያ ቤታቸው (ለምሳሌ፣ በአሜሪካ) ያላቸው ድርጅቶች ማመልከት አይችሉም።

- **ድርጅቴ ከዘመናዊ ባርነት ወይም ከብዝበዛ በሕይወት የተረፉ ሰራተኞች የሉትም፣ ነገር ግን በሕይወት የተረፉትን በፕሮግራሞቻችን እንደግፋለን። ስለዚህ ማመልከት እችላለሁ?**

  **ማመልከት አይችሉም**፣ ምክንያቱም የዚህ ፈንድ አላማ ከዘመናዊ ባርነት ወይም ከብዝበዛ በሕይወት የተረፉ ሰዎችን በመሪነት ቦታዎች ላይ የቀጠሩ ድርጅቶችን ማበረታታት እና መደገፍ ነው።

- **ድርጅቴ መመዝገብ አለበት?**

  ድርጅትዎ መመዝገብ አያስፈልገውም፤ ነገር ግን ድርጅትዎ በመመዝገብ ሂደት ላይ መሆኑን ማሳየት ወይም ድርጅትዎ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ለመመዝገብ እንደሚሰራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማሳየት አለብዎት።

- **እኔ ከዘመናዊ ባርነት እና ከብዝበዛ በሕይወት የተረፍኩ ሰው ነኝ፣ ነገር ግን የድርጅት አካል አይደለሁም - ስለዚህ እንደ ግለሰብ ማመልከት እችላለሁ?**

  **ማመልከት አይችሉም**፣ ይህ ድጋፍ ድርጅቶችን ለመደገፍ ያለመ ፈንድ ነው፣ ስለዚህ በድርጅት ውስጥ ያልተቀጠሩ እና በአመራር ቦታዎች ላይ እየሰሩ ያልሆነውት ግለሰቦችን መደገፍ አንችልም።

- **ይህን ማመልከቻ መሙላት እና ማስገባት ያለበት ከዘመናዊ ባርነት ወይም ከብዝበዛ በሕይወት የተረፈ ሰው ብቻ መሆን አለበት?**

  **መሆን የለበትም**፣ ማንኛውም የድርጅቱ ሰራተኛ ማመልከቻውን በመሙላት እና ማስገባት ይችላል።

- **ተዓማኒ የሆነ የበየነ መረብ አገልግሎት የለኝም፤ ስለዚህ ይህኒን ማመልከቻ በወረቀት በመሙላት ወይም መኢሜል ማመልከት እችላለው?**

  **አዎን ማመልከት ይችላሉ፣** እባክዎ በዚህ ኢሜል SLF@freedomfund.org አድራሻ ኢሜል በማድረግ የማመልከቻ ቅጽ ማግኘት ይችላሉ። የማመልከቻ ቅጹን በጊዜው እንድያገኙ የተሻለውን መንገድ ለመለየት/ለማወቅ ከእርስዎ ጋር እንሰራለን።

- **ስለ ማመልከቻዬ ከፍሪደም ፈንድ መስማት የምችለው መቼ ነው?**

  የማመልከቻው የመጨረሻ ቀን ማመልከቻዎን በበየነ መረብ አማካይነት ወይም በኢሜል በተሳካ ሁኔታ ከመለከቱ/ካስገቡ፣ ለአመልካቾች ስለ ማመልከቻቸው በአንድ ወር የግዜ ገደብ ውስጥ ግብረ መልስእንሰጣለን። እርስዎ ከተመረጡ ማሳወቂያ መልዕክት ይደርሰዎታል፤ የተመረጡ ድርጅቶች ለቃለ-መጠይቅ ይጋበዛሉ። እንዲሁም ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይችላሉ። ከቃለ መጠይቁ በኋላ፣ ማመልከቻዎ የተሳካ ከሆነ የማሳወቂያ መልዕክት ይደርሰዎታል።

THE FREEDOM FUND

## ማመልከቻዬ ቢሳካ ምን ይሆናል?

የተመረጡ ድርጅቶች ስለ ድርጅታቸው፣ የባንክ ሂሳብ መግለጫ እና ስለ ድርጅቶቻቸው ስራዎች መናገር የሚችሉ ከተጠቀሱት ከሁለቱ ሰዎች ተጨማሪ አንዳንድመረጃዎችን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። የተጠየቀው መረጃ ከተሰጠ በኋላ ፍሪደም ፈንድ **የድጋፍ ስምምነት ይልካል፤** ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ገንዘቡ ይለቀቃል። ይህ ሂደት ብዙውን ጊዜ **ከ6-8 ሳምንታት** ይወስዳል፣ ነገር ግን አስፈላጊ መረጃዎችን ወይም ማጣቀሻዎችን ለማቅረብ መዘግየት ሁኔታዎች ከተስተዋሉ፣ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችላል።